# ጭንቀት የወለደው የጦርነት ነጋሪት

## የኤርትራ አጀንዳ እስከመቼ የኢትዮጵያ ህዝብ ዕዳ ሆኖ ለዘላለም ይኖራል?

ከበላይ ገሰሰ

መቋጫ የሌለው የኢትዮ ኤርትራ ጉዳይ አጀንዳ በአፍሪቃ አህጉር ተወዳዳሪ የሌለው የተራዘመና የተወሳሰበ አውዳሚ ጦርነት ቁጥር ስፍር የሌለው የኢትዮጵያውያን ህይወት በልቷል፣ ብዙ ንብረትና ሀብት አውድሟል፣ ባጠቃላይ በኤርትራ ከርሰ ምድር የኢትዮጵያውያን አፅም ያልተቀበረበት መሬት የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ጥያቄው ቀይ ደም የተከፈለበት ቀይ ባህር ለምን ወደብ አልባ የሆነች ሽባ ሀገር ይዘን ቀረን? ይህ ትውልድ ለምን ሃላፊነቱንንና አደራውን አልተወጣም? አሁንስ የኤርትራ ችግር ከራሳችን የሚወርደው መቼ ነው? 85 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ 3 ሚሊዮን ለማይሞላ ህዝብና የፍየል ግንባርን ያህል ለማትሆነው የኤርትራ ምድር እስከመቼ የሰው ህይወትና ንብረት እየገበረ ይኖራል? ለዚህ ሁሉ ውድመት፣ ሽንፈትና ሐፍረትስ ተጠያቂው ማን ነው? ሰሞኑን እየተጎሰመ ያለው የጦርነት ነጋሪትስ ምን ፋይዳ ይኖሯል? የሚሉና ሌሎች በዚሁ አጭር ፅሑፍ ለማየት እሞክራለሁ።

## ከጦርነቱ በስተጀርባ ማን አለ?

ኢትዮጵያ በአፍሪቃ ቀንድ ባላት ስትራተጂያዊ አቀማመጥ፣ በነበራት የቀይ ባህር መተላለፊያ በርና እምቅ የማዕድን ሀብት ክምችት፣ የአባይ ወንዝ ምንጭ፣ ሌሎች የተፈጥሮ ሀብትና የህይማኖት ስብጥር ዓረቦቹን ጨምሮ የባዕድ ወራሪዎችና ቅኝ ገዢዎች ሲመኙዋትና ሲፈታተኑዋት መቆየታቸው ታሪክ ይናገራል። ህዝብዋም በየጊዜው ባድረገው ፀረ ወራር መራራ ገድልና በከፈለው መስዋእትነት በአፍሪቃ አህጉር የነፃነት ደሴት እየተባለች የምትጠራ አፍሪቃዊት ሀገር ኢትዮጵያ ለዚሁ ትውልድ ለማስተላለፍ በቅቷል። ይሁን እንጂ የባዕድ ወራሪዎች ኢትዮጵያን እንደ ሌሎች የአፍሪቃ ሀገሮች በቀጥተኛ ቅኝ አገዛዝ አስገብረው በሀይል ረግጠው ለመግዛት ሲያቅታቸው የተከተሉት አዲስ ስልት በእጅ አዙር ማዳከም፣ በአካባቢው ለርስ በርስ ግጭት የሚጋብዝ ውል መፈፀም፣ እነሱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠሯቸው ሀገር በቀል ሀይሎች ማደራጀት፣ ማስታጠቅና ማሰማራት ነው። ለምሳሌ ግብፅ ኢትዮጵያን አዳክማና በታትና የጥቁር አባይ ወንዝን ምንጭ ለመቆጣጠር በነፃነት ስም እነ ዑስማን ሳሊህ ሳቤን ፈጠረች። እነ ሶሪያ፣ ኢራቅና ሳውዲ የመሳሰሉት ሀገሮች ደግሞ ከህይማኖት ጋር በተያያዘ ሰሜናዊ ክፍል ኢትዮጵያን በዓረብ ዓለም ካርታ በማስገባት አረባዊት ኤርትራ የሚል ስያሜ በመስጠት እነ ጀብሃ ሲረዱ መቆየታቸው ይታወሳል። ፈረንሳይ ጂቡቲን፣ ኢጣሊያ ቀይ ባህር አካባቢን፣ ወዘተ በሀይል በመቆጣጠር ኢትዮጵያ የባህር በር እንዳይኖራት በተደጋጋሚ በታሪክ እንድትቀጣ ከማድረጋቸውም በላይ ዙሪያዋ ሁሉ በጥላቻ አጥረው ውስጡዋም በእርስ በርስ ግጭት እየታመሰች የምትኖር ሀገር እንድትሆን የማያባራ ፈንጅ ቀብረው ሂዷል።

የነዚህ ውስብስ የመቶ ዓመታት መተናኮል ድምር ውጤት ኤርትራ ተገነጠለች። ኢትዮጵያም ያለ ባህር በር ጎራዳ ሀገር ሆና ቀረች። የባዕዳን ህልምም ተሳካ። ደርግም ከስልጣን ተወገደ። ሰራዊቱም ተበተነ፡ በምትኩ “ለኤርትራ ነፃነት ከኤርትራውያን በላይ ሆኖ የተዋጋ”፣ የኢትዮጵያውያን ትጥቅ ሲያስፈታ የቆየ፣ ከባዕድ ጎን ተሰልፎ ወገኑን ሲገድልና ሲፋለም የነበረ፣ በትግራይ ህዝብ ስምና ለጋ ወጣቶች ደም ሲነግድና ሲያስማማ የነበረ የአቶ መለስ ዜናዊ ፀረ ኢትዮጵያ ድርጅት (ህወሓት) በትረ ስልጣኑን ተቆጣጠረ። ህወሓት፣ ኦነግና ሻዕቢያ የተካፈሉበት የሽግግር ጉባኤ በማካሄድ ያለፈው የመቶ ዓመት አጀንዳ ፋይሉ ተዘጋ። ከዚያን ቀን ጀምሮ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ምርኮኛ ተቆጥሮ በፀረ አንድነት ሀይሎች ቁጥጥር ስር ገብቶ እንዳይናገር አፉ ተሸብቦ፣ በገዛ ሀገሩ የቁም እስር ተፈርዶበት የህወሓትና የሻዕቢያ መሪዎች መጫወቻና ቂም መወጣጫ ሆኖ ይገኛል።

ኤርትራ ነፃ ከወጣች በኋላ የህወሓትና የሻዕቢያ መሪዎች ትልቁ ስራ የሆነው ኢትዮጵያውያን በሉዓላዊነታቸው፣ በዳር ድንበራቸውና በባህር በራቸው ዳግም ጥያቄ እንዳያነሱ ሕጋዊ ሽፋን በመስጠት ቀዳዳዎችን ሁሉ መድፈን፣ ታሪክን ማጣመም፣ ኢትዮጵያዊነት ወኔን መግደል፣ በተለይም ወጣቱ ትውልድ ማንነቱን፣ ሀገራዊ ፍቅርንና ነፃ አመለካከትን ሰንቆ እንዳያድግ በውሸት ፕሮፓጋንዳ መመረዝ፣ ባጠቃላይ የቀረችውን ኢትዮጵያ ማዳከምና መበታተን ነው። የዚሁ ተልእኮ ዋና ተዋናይ በመሆን የቀጣዩ የመቶ ዓመት የቤት ስራውን የተቀበለው ደግሞ አቶ መለስ ዜናዊ ነው። በመሆኑም የመንግስት ስልጣኑን መከታ በማድረግ በሀገርና በህዝብ ላይ ከፈፀማቸው የክሕደት ስራዎች ውስጥ ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉትን መጥቀስ ብቻ በቂ ነው።

- የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ዕጣ ፋንታ የተጨረሰው በአሜሪካዊው ሄርሞን ኮሀን ሸምጋይነት አቶ መለስ፣ የኦነግና የሻዕቢያ መሪዎች በተገኙበት ቀደም ብሎ በሎንደን ከተማ በተደረገው ኮንፈረስ ቢሆንም ተንኮላቸውን እንዳይታወቅ ሕጋዊ ልባስ ለመስጠት ለኤርትራ መገንጠል የይስሙላ ሪፈረንደም እንዲካሄድ በማድረግ በህዝብ የተመረጠ ሕጋዊ መንግስት ገና ሳይቋቋም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የኤርትራ ነፃነት በጓሮ ፈርሞ አፅድቋል።
- ከሻዕቢያ ጋር ኢትዮጵያን አብረን እንዝረፍ በሚል አላማ የሀገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም አሳልፎ ሰጥቷል።
- ሻዕቢያ ጠላቶቹ የሚላቸውን ሰዎች ከኢትዮጵያ እያፈነ ወደ ኤርትራ በመውሰድ ደብዛቸው እንዲጠፋ መተባበሩ ብቻ ሳይሆን በኤርትራ በሻዕቢያ እጅ የነበሩት የቀድሞ ሰራዊት ምርኮኞችም አስታዋሽ ወገን አጥተው ደምፃቸ ጠፍቶ እንዲቀር ተደርጓል።
- በፈረንጆች አቆጣጠር ከ1998–2000ዓ.ም በፊት ሻዕቢያ ኢትዮጵያን ለመውረር እየተዘጋጀና በዳር ድንበሩ አካባቢ ህዝብን እያሰቃየ መሆኑን እያታወቀ ጆሮ ዳባ በማለት በተለይም የትግራይን ህዝብ ለወራሪ አሳልፎ በመስጠት ሁለት ጊዜ ገድሎታል።

- በፈረንጆች አቆጣጠር ከ1998 – 2000ዓ.ም ከሻዕቢያ ጋር በተካሄደው ሀገር የማዳን ፍልሚያ እነአቶ መለስና እነ በረከት ስምኦን ጦርነቱ እንዳይሰካና ግቡ እንዳይመታ በጓሮ ሆነው መሰናክል በመፍጠር ትልቅ ሀገራዊ ክሕደት ፈፅሟል።
- ከወራሪ ሻዕቢያ ጋር የተደረገው ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት እንዳይጠቃለል ሆን ብለው ነገሩን በማጣመምና በማደናገር አጀንዳው ወደ ሄግ ፍርድ ቤት እንዲሄድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተባብሯል። የተሰጠው ፍርደ ገምድል ውሳኔም በመሰረተ ሃሳቡ ተቀብለናል ብሎ ባድመን ለሻዕቢያ ለመሸለም ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። አሁንም በረቀቀ መልኩ እየሰራ ይገኛሉ።
- በወቅቱ በሻዕቢያ ወረራና በአቶ መለስ ሀገራዊ ክሕደት የተቆጣው የኢትዮጵያ ህዝብን ለማታለልና የነበረውን ተቃውሞ ለማብረድ ሲባል ባድመ ለኛ ተስጥቷል በማለት በግልፅ በአደባባይ ዋሽቷል። ለዚህም አንድ ቀን እንኳን ይቅርታ አልጠየቀም።
- የኤርትራ ጉዳይ ሕጋዊ ሽፋኝ ለመስጠትና ዳግም ጥያቄ እንዳይነሳ ለማድረግ የሚደረገው ሩጫ በዚህ ብቻ አላበቃም። ባለፈው ዓመት ኢሳያስና የጂቡቲ መንግስት በሁለቱ አዋሳኝ ድንበሮች የሚገኘው የአፋር መሬት በሆነው በራስ ደመራ አካባቢ በተፈጠረው ግጭት ሳቢያ በካታር መንግስት ሽምጋይነት ኢትዮጵያን በማግለል የተፈራረሙትን ውል በባህር በራችን ዙሪያ የይግባኛል ጥያቄ እንዳይነሳ መንገዱን የማጥበብ ሴራ እየተፈፀመ ይገኛል።

# ዛሬስ ጦርነት ማን ከማን ጋር?

ሰሞኑን በአፋር ክልል በውጭ ዜጎች ላይ በደረሰው አደጋ በማያያዝ በተለያዩ የዜና ማሰራጫ ዜዴዎች ተደጋግሞ እንደተገለፀው የአቶ መለስ ዜናዊ መንግስት ሽብርተኞች በሚላቸው ድርጅቶችና በኢሳያስ መንግስት ላይ ያነጣጠረ የተለመደው የማስፈራራትና የሞቅ ሞቅ ፕሮፓጋንዳ ሲያስተላልፍ ሰንብቷል። በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መ/ቤት በኩል በተላለፈው መግለጫ እንደሚያመለክተው “ኢትዮጵያ ራሱዋን ለመከላከል በኤርትራ ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ትገደዳለች” የሚል ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ሰዎች የተለያየ አስተያት ሲሰነዝሩ ቆይቷል። አንዳንዶቹ “የመለስ አስተዳደር የታገቱትን ሰዎች ለማስፈታት ሲል የሚያደርገው ማስፈራሪያ እንጂ በአሁኑ ጊዜ በኤርትራ ላይ ጦርነት ለማካሄድ አይችልም። አቶ መለስ ጦርነት ለማካሄድ የሞራል ብቃት ቢኖረው ኖሮ በአካባቢው ጥቃት ሲደርስ ዛሬ የመጀመሪያው አይደለም። በተለይም በትግራይ በየጊዜው በሰላማዊ ህዝብ ላይ የሚደርሰው የቦምብ ጥቃት መልስ ለመስጠት ቀርቶ በዜና ማሰራጫ በኩል እንዳይተላለፍ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳያውቀው ይደብቁት እንደነበር እሙን ነው” ዛሬ ግን ፈረንጆች ስላሉበት ለዓለም ይፋ መሆኑ ስለማይቀር ምዕራባዊያንን ለማስደሰት ብለው ነው” ይላሉ። ሌሎቹ ደግሞ ሁኔታው ጫፍ ላይ ስለደረሰ ጦርነት ሊካሄድ ይችላል ባዮች ናቸው። ነገር ግን ምን ዓይነት ጦርነት ሊሆን ይችላል? ለሚለው ጥያቄ ብዙ የሚገፉበት አይደለም። ያም ሆነ ይህ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት እያነፋሰው ያለው የጦርነት ከበሮ ምን ያህል እውነትን ይነሯል? የሚለውን መልስ ለማግኘት በሁለቱም ሀገሮች ያለው ሁኔታ በአጭሩ እንመልከት።

**በኢትዮጵያ በኩል** ያለው ገፅታ ስናይ የህወሓት አመራር ለሁለት ከመከፈሉ በፊትና ከተከፈለ ወዲህ ያለው ሁኔታ የተለየ ነው። ቀደም ሲል በድርጅቱ አመራር ውስጥ ቢያንስ የተለያዩ አመለካከቶችና የፓሊሲ ልዩነቶች በመጠኑም ቢሆን የሚንሸራሸሩበት ትንሽ ክፍተት ነበር። ከተከፋፈሉ በኋላ ግን ስልጣን የያዘው የአቶ መለስ ዜናዊ ቡድን በወሰደው የማፅዳት ዘመቻ ብዙ ነገሮች ተቀያይሯል። በሰራዊቱ፣ በመንግስት መዋቅሮች፣ በህወሓት/ኢሕአዴግ ድርጅቶች፣ በሲቢልና ህዝባዊ ተቋማትም ሳይቀር ከአንጃ ጋር ወይም ደግም ከቅንጅት ጋር ንክክ አላቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በማፅዳት በአዳዲስ ታማኝ ግለ ሰቦች ተተክቷል። ከዚያም አልፎ ቁልፍ በሆኑ የስልጣን ቦታዎች በከፊል ወይም በሙሉ የኤርትራ ትውልድ ባላቸው ሰዎች ተይዟል። በድርጅቱና በአባላት፣ በመሪዎችና በሰፊው አባላት መካከል ያለው ትስስርም በአላማ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን አብዛኛው በጥቅም ላይ የተሳሰረ ነው። ባጠቃላይ ስልጣን ከድርጅት ወደ ቡድን፣ ከቡድን ወደ ቤተሰብ፣ መጨረሻም ከቤተሰብ ወደ አንድ ፈላጭ ቆራጭ የአቶ መለስ ዜናዊ ብቸኛ አመራር የተሸጋገረበት ደረጃ ላይ ነው ያለው። ስለዚህ ኢትዮጵያ በኤርትራ ላይ ጦርነት ታካሂዳለች ወይስ አታካሂድም? ለሚለው ጥያቄ መልሱ በአቶ መለስ ዜናዊ እጅ ነው ያለው። ከአቶ መለስ ሌላ ጦርነት ማድረግ አለብን ወይም መካሄድ የለበትም ብሎ በነፃ ሃሳብ ሊከራከር የሚችል የድርጅቱ አባል፣ የመንግስት ባለስልጣን፣ የፓርላማ አባልና ሰራተኛ የለም ማለት ይቻላል። ነፃ ሃሳብ ያለው ሰው ቢኖር ኖሮ በተደጋጋሚ የቦምብ ጥቃት ሰላማዊ ህዝብ ሲያልቅ ይተነፍስ ነበር።

ጦርነት ይካሄድ አይካሄድ በአቶ መለስ እጅ ቢሆንም አቶ መለስ ደግሞ በኤርትራ ላይ ያለው አቋምና ጥብቅና ከላይ በዝርዝር ታይቷል። ቀደም ብሎ ራሱ እንደተናገረው እውነት ከሆነ አቶ መለስ በሚቀጥለው ምርጫ እንደማይወዳደር ነው የሰማነው። የስልጣን ዘመኑ መጨረሻ እየተቃረበ በሄደ ቁጥር ደግሞ ያስጠይቁኛል የሚላቸውን ቀዳዳዎች ሁሉ እየደፈነ ነው ያለው። ለምሳሌ በቀድሞ የደርግ ባለስልጣናት ላይ የወሰደው የይቅርታ እርምጃ በተመሳሳይ ከኤርትራ ጋር ያለው ውጥረትም ከስልጣን ከመሰናበቱ በፊት በእርቀ ሰላም ይጨርሷል የሚሉ አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ከኢሳያስ ግትርነት ጋር ተያይዞ በኢትዮ ኤርትራ ያለው ውጥረት ወደ ተጋጋለ ሁኔታ ስለደረሰ በጦርነት እንጂ በሰላም የሚጨረስበት ጊዜ አልፏል የሚሉም አሉ። በአቶ መለስ መልካም ፍቃደኝነት በኢትዮጵያ ምድር እየተንቀሳቀሱ ያሉ የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች የአቶ ኢሳያስ አመራርን ይተካሉ የሚል ግምት ስላላቸው ጦርነቱ አይቀሬ ነው የሚሉም አይጠፉም። ስለሆነም አቶ መለስ ሁለት ምርጫ ነው ያለው። አንዱ ባድመን ለሻዕቢያ አስረክቦ በእርቅ መገላገል ነው። ሌላው አማራጭ ሻዕቢያ በተባበሩት መንግስታት ማዕቀብ ተጥሎበት በውጥረት ላይ እያለ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ጦርነት ማካሄድ ነው። የተጠቀሱትን አማራጭ ሃሳቦች እንዳሉ ሆኖ ጦርነት ይካሄዳል ብለን ብንነሳ ከዚህ ጋር ተያይዘው መነሳት ያለባቸው ጥያቄዎች ግን አሉ።

- የኢትዮጵያ ሰራዊት ጦርነቱን በአሸናፊነት ለመወጣት የሚያስችለው የሞራል ብቃትና ዝግጅነት አለው ወይ? የአቶ መለስ አገዛዝ በህዝብ ላይ እየፈፀመ ያለው አፈናና የማሸበር ተግባር ሰራዊቱን አይነካም ወይ? በአቶ መለስ ላይስ ምን ያህል እምነት አለው?

- አቶ መለስ በኤርትራ ላይ ጥቃት ለማድረግ የሚያስችል ከፊቱ የተለየ የአመለካከትና የፓሊሲ ለውጥ ማድረግ ይችላል ወይ?
- የሚካሄደው ጦርነትስ እስከ ምን ድረስ ነው? ሻዕቢያን ለመደምሰስ ወይስ አስገድዶ ወደ ድርድር ለማምጣት? ካሁን በፊት ከሻዕቢያ ጋር ከተደረገው ጦርነት የአሁኑ በምን ይለያል? ጦርነቱስ ምን ያህል ጊዜ ሊፈጅ ይችላል?
- እነ አቶ መለስ በኤርትራ ላይ ጦርነት ቢያካሂዱ የሁለቱን ህዝብ ዘላቂ ሰላምና ጥቅም ሊያመጣ ይችላል ወይ?
- ኢትዮጵያ በኤርትራ ላይ ጥቃት ለማካሄድ ዓለም አቀፍ ሕግ ይፈቅድላታል ወይ?
- በሀገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የፓለቲካ ድርጅቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ያላቸው አቋምስ ምንድን ነው? ተቃዋሚ ድርጅቶችን ሳያማክርና ሳያሳተፍ የሚካሄድ ጦርነትስ ውጤት ሊኖረው ይችላልን?

የሚሉ ጥያቄዎች ተጨባጭ መልስ የሚሹ ወሳኝ ጉዳዮች ቢሆኑም በዚሁ ፅሑፍ በዝርዝር የምንሄድበት ሳይሆን እነሱ እንደሚሉት ምናልባት ወደፊት ጦርነቱ ከተጀመረ ትያትሩ አብረን ሁላችንም በቅርብ የምንከታተለው ነው የሚሆነው።

**በኤርትራ በኩል** ያለው ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ ብዙ ነገሮችን መገንዘብ እንችላለን። የአቶ ኢሳያስና የአቶ መለስ አገዛዝ ምናልባት በቦታና በመልክ ይላያዩ ይሆናል እንጂ ባህሪያቸው፣ ታሪካቸውና ተግባራቸው ሲታይ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅ ናቸው። ሁለቱም ለኢትዮጵያ አንድነትና ህልውና ጠንቅ ናቸው ብቻ ሳይሆን ለአፍሪቃ ቀንድ ህዝቦች ሰላም፣ ዕድገትና መልካም ጉርብትናም አደጋ ናቸው። ሁለቱም ወደ ስልጣን የመጡት በምርጫ ሳይሆን በአፈ ሙዝ ስለሆነ አሁንም ስልጣናቸውን የሚጠብቁት በሕግ ልዕልና ሳይሆን በአፈ ሙዝ በማስፈራራት፣ በማፈን፣ በመግደልና በህዝብ መካከል ግጭት በመጫር ነው። ሁለቱም አንዴ እጃቸው በደም ስለተነከረ ያላቸው ምርጫ ከህዝብ ጋር ተደራድሮ በሰላም መኖርና ስልጣን ለህዝብ ማስረከብ ሳይሆን እስከ መጨረሻ በመላላጥና ወገን ከወገኑ ጋር በማጨፋጨፍ አጥፍቶ መጥፋትን ነው የሚመርጡት። ሁለቱም የተፈጠሩትና ያደጉት በህዝብ ፍላጎትና ይሁንታ ሳይሆን ለባዕዳን ስትራተጂያዊ ፍላጎትና አላማ ማስፈፀሚያ ስለሆነ በአካባቢያቸው ያለው ችግር ለመፍታት የሞራል መሰረት የላቸውም። ከዚህ ሰይጣናዊ ባህሪያቸው የተነሳ ለረዥም ዘመናት በታሪክ፣ በባህል፣ በስነ ልቦናና በደም የተሳሰረና የተዋለደ ህዝብ የውሸት ታሪክ ፈጥረው አንድ ቤተ ሰብ ሳይወድ በግድ ለሁለት እንዲከፈል በማድረግ ኤርትራን ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል አድርጓል። ይህ በዘመናችን የተከሰተ አሳዛኝ፣ አውዳሚና ደማዊ ጦርነት ምንጩ ህዝቡ ሳይሆን የሻዕቢያና የህወሓት መሪዎች መሆናቸው ኤርትራውያን፣ ኢትዮጵያውያንና የዓለም ማሕበረሰብም ጭምር የሚያውቀው ጉዳይ ነው።

ሁላችንም እንደሰማነውና እንደተገነዘብነው ለዓመታት ያህል እነ አቶ መለስና ኢሳያስ ሲነግሩን የነበረ "በጦርነት ከመኖር ይልቅ ኤርትራ ብትገነጠል የኤርትራ ህዝብ ነፃነት ያገኛል፣ የኢትዮጵያ ህዝብም እፎይታና ሰላም ያገኛል" የሚል እንደነበር ይታወሳል። ነገር ግን በተግባር ሲታይ የባሰ እንጂ የተሻለ ሆኖ አልተገኘም። ሁለቱም መሪዎች የኤርትራ ህዝብ ነፃ አውጪና ባለውለታ መስለው ለመመፃደቅ ቢሞኩሩም የኤርትራ መገንጠል ከማንም በላይ የጎዳው የኤርትራ ህዝብ ራሱን ነው። ኤርትራ መሬትዋን እንጂ ህዝቡ ገና ነፃ እንዳልወጣ በሀገሪቱ ላይ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ራሱ ቁልጭ አድርጎ ያስረዳል። ኤርትራ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ የሰው ልጅ በእስር የሚሰቃይባት፣ አንድ ጨካኝ፣ ኋላ ቀር፣ ፈላጭ ቆራጭና ጦረኛ መሪ የነገሰባት፣ ዜጎችዋ በስደት እየተንከራተቱ አሳረ መከራቸውን የሚያዩበት፣ ህዝብዋ በስመ ነፃነት ወደ ባርነት፣ ውርድትና ልመና የገባበት የአፈናና የትርምስ ሞዴል ናት ቢባል ማጋነን አይሆንብኝም። ከሁሉም በላይ የሚገርመው ግን በሀገሪቱ ያለው ፍርሃት፣ ረሃብና ጭቆና ብቻ አይደለም። ከሰላሳ ዓመታት በላይ ለሰው ልጅ ነፃነት ታግለናል የሚሉ መሪዎች በአሁኑ ዓለም በሰለጠነበት በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ላይ ሆነው ሀገሪቱን ያለ ሕገ መንግስት በድሮ <u>በጫካ ሕግ</u> የምትገዛ ሀገር መሆንዋን ነው። አምባ ገነኖች ህዝቡን አደንቁሮ፣ አሸብሮ፣ አንደንዝዞና አደናግሮ መግዛት ዋነኛ የመጨቆኛ መሳሪያቸው መሆኑን ከኤርትራ በላይ ሌላ ምስክር አይኖርም። ታዲያ! የነፃነት ትርጉም የተሳሳተው ከመዝገበ ቃላቱ ነው? ወይስ መለስና ኢሳያስ ናቸው ያለ ትርጉሙ የሰጡት?

አቶ መለስ ዜናዊ በእናቱ ኤርትራዊ መሆኑን የቅርብ ዘመዶቹና አብሮ አደግ ጓደኞቹ ይናገራሉ። አቶ ኢሳያስ አፈ ወርቂም እናቱ በዓድዋ አካባቢ የምትገኘው "ይሓ" የምትባል ታሪካዊት ቦታ የተወለዱ ትግራወይቲ መሆናቸው የአካባቢው ህዝብ ይናገራል። ታዲያ እነዚህ መሪዎች ሁለቱን ህዝብ ተፋቅሮና ተከባብሮ በሰላም እንዲኖር ከማድረግ ይልቅ መገነጣጠልን ለምን መረጡ? ከሰላም ይልቅ ጦርነት እንደ ዋነኛ ስራቸው አድርገው የወሰዱበት ምክንያትስ ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ ላንዳንዶቻችን ሊገርመን ይችላል። ለኔ ግን አይገርመኝም። ምክንያቱም አምባ ገነኖች ለስልጣናቸው፣ ለህልውናቸውና ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ህዝብና ሀገር ቀርቶ የስጋ እናታቸውም ጭምር ለባዕድ ለማስማማት ወደኋላ እንደማይሉ እሙን ነው። ስለዚህ አቶ ኢሳያስና አቶ መለስ ነጋ ጠባ በጦርነት ከበሮና በክተት ጥርምባ የሚያደነቁሩን ለህዝብና ለሀገር አስበውና ተቆርቁረው አይደለም። ጦርነቱን የሚጭሩበትና የሚመርጡበት ዋናው ምክንያት አንደኛ የህዝብ ውጥረትና ተቃዉሞ ሲበዛባቸው እንደ ቀልብ መሳቢያና የህዝቡን ትኩረት ማስቀየሪያ አድርገው ይጠቀሙበታል። ሁለተኛው ምክንያት የተቃውሞ ሀይል ሰበብ አስባብ ፈለግው ለመምታት ሲፈልጉ ጦርነት እንደ ማስፈራሪያና አብሮ መደቆሻ አድርገው ይጠቀሙበታል። ሶስተኛው ምክንያት የባዕድ ሀይል ተልእኮ በማስፈፀም ጉርሻ ለማግኘት ነው። አራተኛው ምክንያት የሰላም ባህርይ፣ የሀገርና የህዝብ ፍቅር የላቸውም። በጦርነት ምንክያት የሚያልቀው፣ ቤት ንብረቱ የሚፈርሰው፣ የሚቆስለው፣ የሚሰቃየው፣ የሚፈናቀለውና የሚሰደደው የድሃው ልጅ እንጂ እነሱን አይነካም። በደርግ ጊዜ "የድሃ ልጅ ወደ ባሌ የሃብታም ልጅ ወደ ቦሌ" እየተባለ ይነገር እንደነበር ሁሉ ዛሬም የባለስልጣናትና ካድሬ ልጆች በአሜሪካ፣ በአውሮጳና በነቻይና ከተሞች በምርጥ ት/ቤቶች ሲማሩ የመከረኛው ድሃ ህዝብ ልጆች ግን ደማቸውና አጥንታቸው በሳሕል፣ በባድመ፣ በፆሮና፣ በዛላምባሳና በዓይጋ ተራሮች ተከስክሶ ከመቃብር እየጮኸ ይገኛል። ባለስልጣናትና አጃቢዎቻቸው የህዝብና የሀገር ሀብት ዘርፈው ፎቅ ሰርተው ሲንደላቀቁ የድሃ ልጅ ግን በጦርነት ምክንያት በሞቋድሾ ከተማ ሬሳው በአደባባይ ሲጎተት ማየቱ ምን ያህል ዘገናኝ እንደሆነ የህዝብ ወገን የሆነ ሁሉ ይገነዘቧል።

ዛሬ በኤርትራ በኩል ያለው ሁኔታ ስንመለከት ምናልባት ጦርነቱ ቢጀመር ራስዋን ለመከላከልና ለመመከት የሚያስችል ዓቅምና ሁኔታ አላት ወይ? የሚለው ጥያቄ እንዳናነሳ ያስገድደናል። ድሮ ከሻዕቢያ በስተጀርባ ሆነው ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለመበታተን አይዞህ ሲሉ የነበሩ እንደነ ሊቢያና ግብፅ የመሳሰሉ ሀገሮች ዛሬ ኤርትራን መርዳት ቀርቶ ለራሳቸው በምን ሁኑታ ላይ እንዳሉ እያየነው ነው። ድሮ ሻዕቢያን በመደገፍ በቀይ ባህር አካባቢ ያለውን ጂኦ ፓለቲካዊ ጥቅማችንን እናስከብራለን ብለው ተስፋ ሲያደርጉና ሲደግፉ የነበሩ አንዳንድ ምዕራባዊያን ሀገሮችም ዛሬ ፊታቸው አዙሯል ብቻ ሳይሆን በተባበሩት መንግስታት በኩል በኤርትራ ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ እንዲደረግ ከሚገፋፉ ሀገሮች ዋነኞቹ ናቸው። የአፍሪቃ አንድነት ድርጅትም ሆነ የኢጋድ አባል ሀገሮች በኤርትራ ላይ ተፅዕኖ እንዲደረግ ደፋ ቀና ሲሉ ከርማል። ከየመን፣ ከጂቡቲና ከሱዳን ያላት ጉርብትናም ብዙም አይመስለኝም። በኤርትራ ውስጥ ያለው የፓለቲካ ሁኔታም ከላይ እንደተጠቀሰው ከማንም ጊዜ በላይ አደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳለ ነው የሚታየው። በተለይም ወጣቱ ወደ ስደት እየጎረፈ እንደሆነ በግልፅ ይታያል። ምን ያህል ዓቅም እንዳላቸው አይታወቅም እንጂ የአቶ መለስ መንግስትም ሻዕቢያን የሚተኩ ሀይሎች እየደገፈና እያደራጀ እንደሆነ እናያለን። በመሆኑም ከነዚህ አዝማሚያዎች በመነሳት ጦርነቱን አስመልክቶ በኤርትራ በኩል ስላለው ጉዳይ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንድናነሳ ሁኔታው የሚጋብዝ ነው።

- በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ጦርነት ቢነሳ የዓለም አቀፉ ሁኔታ ለማን ያመዝናል?
- የሻዕቢያ ሰራዊት ጦርነቱን ለመከላከልና በአሸናፊነት ለመውጣት የሚያስችል ሞራልና ብቃት አለው ወይ?
- ስደትና መንከራተት የሰለቸው የኤርትራ ህዝብ በአሁኑ ጊዜ ጦርነትን መሸከም ይችላል ወይ?
- በሁለቱ ሀገሮች ጦርነት ቢነሳ ሌሎች አጎራባች ሀገሮችስ አይነካም ወይ? የቀይ ባህር ቀጠናስ አይበጣበጥም ወይ?
- ከሻዕቢያ በኋላስ ምን ዓይነት ኤርትራ ልትሆን ትችላለች?
- ጦርነቱ ቢካሄድ በኤርትራ ውስጥ የሚገኙ እንደ ኦነግ የመሳሰሉ ተቃዋሚ ሀይሎች ዕጣ ፋንታቸው ምን ሊሆን ይችላል?

እነዚህ ጥያቄዎች መመለስ ያለባቸው ቁልፍ ጉዳዮች ቢሆኑም በዚሁ አጭር ፅሑፍ በዝርዝር የምናየው አይደለም። ነገር ግን አንድ ነገር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። እሱም አቶ ኢሳያስና አቶ መለስ ዘናዊ በዚች ምድር በስልጣን ላይ እያሉ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ዘላቂ ሰላም፣ ዕድገት፣ መልካም ጉርብትናና የጋራ ጥቅም ይከበራል ወይም ይመጣል ብሎ ተስፋ ማድረግ <u>"ከእባብ እንቁላል እርግብ ይወለዳል"</u> ብሎ እንደ መጠበቅ ያህል ነው። የሀገራችን ገበሬ ሲተርት <u>"ሲሰርቀኝ ያየሁት ቢሰጠኝም አላምነውም"</u> ይላል። ኀበዝ!! ስንት ጊዜ እንሞኝ!! እነዚህ ራሳቸው የጦርነት፣ የርስ በርስ መናቆር፣ የድህነት፣ የስደትና የጭቆና ምንጭ የሆኑት ግራዚያኒ መሪዎች እንደገና ዛሬ የጦርነት አቢጋዝ ሆነው ነጋሪት እየጎሰሙ ህዝብን ለማደናገርና ለማሸበር ቢሞክሩ አብረን የምናጨበጭብ ከሆነ ስህተቱ የነሱ ሳይሆን የምንወቀሰው እኛው ራሳችን ነን። ይህን ያልኩበት ምክንያት ራሳችንን ከጥቃት መከላከል የለብንም ማለቴ አይደለም። ነገር ግን ጦርነቱ የሁለቱን ህዝብ ዘላቂ ሰላም የሚያመጣ መሆኑንና አለ መሆኑን እርግጠኞች መሆን አለብን የሚል ፅኑ እምነት ስላለኝ ነው። ካልሆነ ግን የሁለቱን አምባ ገነን መሪዎች ዕድሜ ማራዘሚያ ተብሎ የሚካሄድ ጦርነት ችግሩን ከማባባስ አልፎ የሚያመጣው መፍትሄ አይኖርም። ይህም በተግባር አይተነዋል። በፈረንጆች አቆጣጠር ከ1998–2000ዓ.ም ከሻዕቢያ ጋር የተደረገው የሞት ሽረት ፍልሚያው አስመራ አፋፍ ላይ ደርሶ በነበረበት ጊዜ በጓሮ ትእዛዝ በማስተላለፍ የሰራዊታችንን ትጥቅ በማስፈታት ሻዕቢያን ከሞት በማዳን እንደገና ተጠናክሮ በህዝባችን ላይ ቦምብ እየጣለ ወገኖቻችን እንዲገድል ያደረገው ማን ነው? ለህዝብና ለሀገር ነፃነት ሲሉ ክቡር ህይወታቸው የከፈሉ የጀግኖቻችን መስዋእትነት ያለ ምንም ውጤት ደመ ከልብ ሆኖ እንዲቀር ያደረገ ማን ነው? በጦር ሜዳ አሸንፈን እያለን ወደ ሄግ ፍርድ ቤት ወስዶ ያንበረከከን ማን ነው? በፍርደ ገምድል ዳኝነት የተወረረ እያለ ወራሪ እንዲሸለም ያደረገስ ማን ነው? የፍርዱ ውሳኔ አስፈፃሚ ሆኖ ሽር ጉድ እያለ የከረመውስ ማን ነው? መልሱ ከሃዲውና ፈርጣጩ መሪ መለስ ዜናዊ ነው ብላችሁ እንደምትመልሱ አልጠራጠርም። ታዲያ!! ነገሩ ግልፅ ሆኖ እያለ ዛሬ ገና ቁስላችን ሳይሽር ሌላ የማታሊያ ካባ ለብሶ ኢሳያስን እዋጋለሁ ብሎ የውሸት ከበሮ ቢመታ በህዝብ ላይ ከማፌዝና ከመቀለድ በስተቀር እውነት ውጤት ይኖሯል ብላችሁ ታምናላችሁን?።

## አሁን ምን ይደረግ?

የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ሰሞኑን በተደጋጋሚ በቴሌቭዥንና በተለያዩ ዜናዎች ለማየቱና ለመስማቱ በሚዘገንን መልኩ የአቶ ኢሳያስ ምስልና ካሁን በፊት በአኬልዳማ ያስተላለፈውን ቪድዮ እያጣቀሰ እንዳሰራጨው "በአሁኑ ጊዜ በኤርትራ ላይ የምንወስደው ራስህን የመከላከል እርምጃ <u>በአንድ ዋንጭፍ ሁለት ወፍ ለመምታት ነው"</u> በማለት ደጋግመው ሲዝቱና ሲናገር ተደምጧል። ትርጉሙም የምናካሂደው ጦርነት ሻዕቢያን ለመምታት ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚ ሀይሉንም ጭምር አብሮ ለመድቆስ ነው ማለት እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው። አዎ!! ራሱን የአፍሪቃ ንጉሰ ነገስት ነኝ ብሎ ይሰይም የነበረው መሐመድ ጋዳፊ በንቀት ተቃዋሚዎችን ዓይጥ እያለ ይጠራቸው እንደነበር አስታውሶኛል። በመጨረሻ ግን ዓይጦች በቆፈሩት ጉድጓድ ነው ተጥሎ የተገኘው። ደርግም በጊዜው ህወሓትን የጓሮ ዓይጥ እያለ ይጠራቸው እንደነበር አስታውሳለሁ። ዛሬም በተመሳሳይ የራሱን ታሪክ እንኳን በቅጡ የማያውቅ አቶ መለስ ዜናዊ ተቃዋሚዎችን አንዴ ተላላኪዎች፣ አንዴ ሽብርተኞች፣ አንዴ ጣታቸው ይቆረጣል፣ ወዘተ እያለ ለሰው ልጅ የውሻን ያህል እንኳን ክብር ሳይሰጥ ከሰብአዊ ርህራሄ አያያዝ ውጭ የግል ስብእናቸውና የእስረኛነት መብታቸው በሚዳፈር መልኩ በዜጎቻችን ህይወት ላይ እየተጫወተ እንደሆነ የብዙ ሚሊዮኖች ኢትዮጵያውያን ልብ እያቆሰለ እንዳለ መገመቱ አያዳግትም። አዎ!! የሰው ልጅ ነፃነትን የማያውቅ ነፃ አውጪ!! ተብሎ የለ!!

ለዚህ ሁሉ መከራ መፍትሔው ጥርስን ነክሶ እህህ!! እያሉ እያለቀሱ መኖር አይደለም። መፍትሄው አምባ ገነኖች በሚለኩሱት እሳትና በሚያጠምዱት ወጥመድ ገብቶ መንፈራገጥም አይደለም። ዋናው መድሃኒቱና መፍትሔው ተደጋግሞ እንደተነገረው አሁንም በእጃችን ላይ ነው ያለው። እሱም በመካከላችን ሊኖር የሚችል መለስተኛ ልዩነቶችን ወደ ጎን ትተን፣ የህዝባችንና የሀገራችንን ጉዳይ በማስቀደም የትግል ግንባር መፍጠር ነው። የአቶ መለስ ዜናዊ አረሜናዊ አገዛዝ በኛ ድክመት፣ በኛ እርስ በርስ መጠላለፍ፣ በኛ ልዩነትና መናቆር ዕድሜው እንዲያራዘምና እንዲጠነክር በምንም መልኩ ዕድል መስጠት የለብንም። ለምሳሌ በቅርብ ቀናት የኦነግ አባላት የወሰዱትን <u>መራራና ቆራጥ እርምጃ</u> እጅግ የሚደነቅ ነው። ይህም ብልጭ ብሎ እንዳይጠፋ መንከባከብ፣ ማበረታታትና ማጠናከር የሁላችንም ሃላፊነት ነው።

“አንድ ሰው የሚያሸንፈው ራሱ ነው” እንደሚባለው ሁሉ አንድነት ወይም ለውጥ ስላልን ብቻ ዝም ብሎ ወደ ቤታችን አይመጣም። እኛ ነን ወደ እሱ መሄድ ያለብን። ስለዚህ ወደ ተግባር ለመሸጋገር ልክ የኦነግ አባላት እንዳደረጉት ሁሉ ከእያንዳንዳችን ቆራጥ ውሳኔና እርምጃ ይጠይቃል። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ፍርሃትን ሰብሮ መውጣት የግድ ይላል። ፍርሃትን ሰብሮ መውጣት ከትጥቅ በላይ ሀይል አለውና ነው። መፍራትና መደንገጥ ያለበት በሀገርና በህዝብ ላይ በደል የፈፀመ እንጂ ለሀቅና ለፍትሕ የቆመ ሰው አይደለም። በቱኒዚያ፣ በሊቢያ፣ በግብፅ፣ በየመንና በሌሎች እየታየ ያለው የህዝቡ ቆራጥ ተሳትፎ በተለይም ሴቶች ተአምር እየሰሩ እንዳሉ በየቀኑ የምናየው ነው። እኛ ኢትዮጵያውያንም መለያችን ጀግንነት እንጂ ፍርሃት ሆኖ አያቅም። መለስ ዜናዊ አንጄ አኬልዳማ ምንትስዬ እያለ የሚያሳየው ቪድዮ አሁን የጀመሩት ሳይሆን ከድሮ ከተፈጠሩበት ቀን ጀምሮ የነበረ የትግራይን ህዝብ ያሰለቸ የአገዛዝ ስልታቸው ነው። በተለይም ምርጫ በተቃረበ ቁጥር አስደንጋጭ የሆኑ ነገሮችን እየፈበረኩ ህዝብን ማሸበር ለረጅም ጊዜ የተካኑበት የነ አቶ መለስ ልዩ ሙያ ነው። ይህ የህዝቡን ስነ ልቦና ለመስለብ ብለው የሚያሳዩት የማስፈራሪያ ቪዲዮና የጦርነት ዳንኬራ ወደው አይደለም። “ንፁህ ደም ከአልኮሆል በላይ ያሰክራል” እንዲሉ በሀገርና በህዝብ ላይ የፈፀሙትን በደል ስለሚያውቁት ዙሪያቸውን ሁሉ ጠላት መስሎ ስለሚታያቸው ከጭንቀት የተነሳ መሆኑን ከፊታቸው ማንበብ ይቻላል። ስለዚህ እነሱ በንቀት ተቃዋሚውን ጎራ ለማዳከምና ለማስፈራራት ሲሞክሩ “እኛም አውቀናል ጉድጓድ ጭረናል” ብለን እነመለስ እንደሚገምቱን ሳይሆን በልጠን መገኘት አለብን እላለሁ።

በተረፈ ለሁላችሁም መልካም ዕድል እመኛለሁ።

አንድነታችን ይለምልም!!

ከበላይ ገሰሰ